M

# 2007-2008 የመካከለኛ ደረጃ ትምህርትቤት ማመልከቻ መመሪያዎች

ለ2007 2008 የትምህርት ዘመን ለማመልከት የመካከለኛ ደረጃ ማመልከቻን ይጠቀሙ። ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት እባክዎትን የ2007 2008 ምዝገባ የወላጆች መመሪያ መጽሄትን ይመልከቱ ወይም የመመዝገቢያ አገልግሎት ማእከልን ይጎብኙ። .

**ክፍል 1 –** ልጅዎ የሚኖርበት አድራሻ ይጻፉ(የቤትዎ አድራሻ)። ልጅዎ የሚኖርበት ከአንድ በላይ የተለያዩ አድራሻ ካለው/ካላት በተለይ በተቀዳሚነት የሚኖሩበትን አድራሻ ይጻፉን።

**ክፍል 2 –** ለ2006 2007 የትምህርት ዘመን ልጅዎ የሚገባበትን የክፍል ደረጃን ይጻፉ

**ክፍል 3 (አማራጭ) –** ወንድም ወይም እህት በሚመሩበት ትምህርትቤት ልጅዎ ለማስመዝገብ የሚፈልጉ ከሆነ ብቻ ይህንን ክፍል ሞምላት ትችላላችሁ። ወንድም ወይም እህት በሚማሩበት ትምህርትቤት ቦታ ለማግኘትና ቅድሚያ ለማግኘት የቤትዎ አድራሻ አንድ አይነት መሆን አለበት። በማህደራችን ተመዝግቦ ያለው የልጅችዎ አድራሻና አሁን በክፍል 1 ላይ የጻፉት አድራሻ አንድ አይነት መሆኑን ማረጋገጥ የርስዎ ሃላፊነት ነው።የተሳሳተ አድራሻ ከሆነ ግን ወንድም እህት በሚማሩበት ትምህርትቤት ቦታ ለመመደብ ልጅዎ ቅድሚያ ላያገኝ ይችላል።በተጨማሪም ወንድም እህተማሞቹ ለ2007 2008 የትምህርት ዘመን በዚያው ትምህርትቤት መመደብ አለባቸው።ወንድምና እህት በሚቀጥለው አመት እዛው ትምህርትቤት የማይማሩ ከሆነ ለወንድምና እህተማማች የሚሰጠውን ቅድሚያ ሊያገኑ አይችሉም።. .

**ክፍል 4 –** ክፍል 4ን ለሞምላት በፎርሙ በስተጀርባ ያለውን የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት የምርጫ ፎርም የሚባለውን ይጠቀሙ። የትምህርት ቤቶቹ ስም በቅደም ተከተል ተዘርዝሮ ተጽፈዋል። የትራንስፖርት አገልግሎት የሚያቀርቡ ወይም የሚሰጡ ትምህርትቤቶችም ስም በእያንዳንዱ ሰፈር ወይም ክልል መስረት ተዘርዝሮ ተጽፈዋል። በከተማው ለሁሉም ስፍራዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡትንም ትምህርትቤቶች ስም ከታች በዝርዝር ተጽፈዋል። መደበኛና ሙሉ ቀን የትምህርት ፕሮግራም ያላቸው ትምህርትቤቶችም ዝርዝር ተጽፈዋል።የስፔክትረም እና የኤፒፒ ፕሮግራም የሚሰጡት ምህርትቤቶችም ስም ለብቻ ተጽፈዋል

በፎርሙ ላይ የሚመርጡትን ትምህርትቤት በቅደም ተከተል ከአንድ እስከ አስር ተራ ቁጥር ድረስ ይጻፉ።የሚፈልጉትን ትምህርትቤት መምረጥ ይችላሉ ሆኖም ግን የሚመርጡት ትምህርትቤት ከክልልዎ ውጭ ከሆነ ልጅዎ የትራንስፖርት አገልግሎት ላያገኝ/ላታገኝ ይችላል/ትችላለች።

ፎርሙን ተጠቅማችሁ በክፍል 4 ላይ <u>ሰዎስት</u> ትምህርትቤቶችና ፕሮግራሞች ይምረጡ። የመጀመሪያ ምርጫዎን የሆነ የትምህርትቤቱ ተራ ቁጥር እንዲሁም የትምህርትቤቱ ስም ይጻፉ። ወደ የስፔክትረም እና የኤፒፒ ፕሮግራሞች ለማመልከት የምትፈልጉ ከሆነ አማራጭ ፕሮግራም በሚለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። ወደ መደበኛው ሙሉ ቀን ትምህርት ፕሮግራም የምታመለክቱ ከሆነ የአማርጭ ፕሪግራም ሳጥን ባዶውን ይተዉት። ከታች ያለው ምሳሌ የሚያሳየው በመምረጫው ፎርም ክፍል 4 እንዴት መሞላት እንዳለበት ነው። ከታች ያለ ምሳሌ እንደሚያሳየው ለምሳሌ የመጀመሪያ ምርጫዎ የሳሚት ትምህርትቤት ሲሆን በሁለተኛው ምርጫ ደግሞ የዴኒ እና በሰዎስተኛው ምርጫዎ ደግሞ የሙሉ ቀን መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም በዴኒ ትምህርትቤት ማለት ነው።

| | School Number | | | School Name | Optional Program: Spec-trum | Optional Program: APP |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 9 | 4 | 2 | Summit | ○ | ○ |
| 2 | 1 | 0 | 3 | Denny | ● | ○ |
| 3 | 1 | 0 | 3 | Denny | ○ | ○ |

**ክፍል 5 (አማራጭ) –** የመጀመሪያ ምርጫዎ የሆነ ትምህርትቤት ልጅዎ ካልተመደበ እሱ ወይም እስዋ ክፍት ቦታ እስከሚገኝ ድረስ በተጠባባቂነት ሊመዘገቡ ይችላሉ። የመጀመሪያ ምርጫዎ ያልሆነ ትምህርትቤት በሌላ ትምህርትቤት ተማሪ ልጅዎ በተጠባባቂነት እንዲመዘገቡ የሚፈልጉ ከሆነም በክፍል 6 ያለውን ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ የሚፈልጉትን የትምህርትቤቱ ስም ይጻፉ። በክፍል 5 ላይ ከተዘረዘሩትን ማናቸውም ትምህርትቤቶች መምረጥ ይችላሉ። ልጅዎ ወደ የመጀመሪያ ምርጫዎ የሆነ ትምህርትቤት በተጠባባቂነት ሊመዘገብ የሚችለው በማመልከቻዎ ላይ ዝቅተኛውን ተራቁጥር ካለው ብቻ ነው። ልጅዎ በተጠባባቂነት መመዝገብ የሚቻለው በአንድ የተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ ብቻ ነው።